# እሰቲ ልጠይቅሽ ?!

አሥራደው (ከፈረንሳይ)

አድምጭኝ አገሬ፤

መመኪያዬ ክብሬ፤

የ'ኔነት መግለጫ ክብርና ኩራቴ፤

የመኖሬ ትርጉም ፍቺ የሕይወቴ፤

ማረፊያ ጎጆዬ ሲደክም ጉልበቴ፤

እሰቲ ልጠይቅሽ፤

ምትክ ለልጆችሽ፤

ላንቺ በደከሙ ላንቺ በሞቱልሽ፤

እነማንን ተካሽ ?!

እነማንን ወለድሽ ?!

በሊጋነት ዕድሜ ገና በጨቅላነት፤

ላንቺ ልዕልና ብለው በተሰውት፤

በነዛ ጉብሎች በነዛ ሰማዕት፤

በወጣት ልጆችሽ፤

እነማንን ተካሽ ?!

እነማንን ወለድሽ ?!

አገሬ ንገሪኝ እሰቲ ልጠይቅሽ ።

ከራሳቸው ሕይወት ላንቺ የሚያደሉ፤

ላንቺ የታመሙ ላንቺ የቆሰሉ፤

*ላንቺ ዘብ በመቆም ላንቺ ተሰውተው፤*

*ተቃጥለው ላለፉ በፍቅርሽ ጧፍ ሆነው፤*

*ለክብርሽ እንደ ሰም ለተነኑ ቀልጠው፤*

*በነዚያ ልጆችሽ፤*

*እነማንን ተካሽ ?!*

*አገሬ ኢትዮጵያ እስቲ ልጠይቅሽ ?!*

*ጀግና ደራሲውን፤*

*መሃንዲስ ሐኪሙን፤*

*ቆፍጣና ወታደር ድንበር ጠባቂውን፤*

*ነጋዴ ገበሬ ተማሪ አስተማሪ፤*

*ሰአሊ ተዋናይ ምሁር ያገር መሪ፤*

*ዳኛ ዲፕሎማት፤*

*መሪ የሃይማኖት፤*

*ሁሉን አሰናብተሽ፤*

*ኧረ ለመሆኑ እነማንን ወለድሽ ?!*

*እነማንን ተካሽ ?!*

*አገሬ ንገሪኝ እስቲ ልጠይቅሽ ?!*

*መካሪ ዘካሪ ምሑር አስተማሪ፤*

*ጀግና ወቶ አዳሪ ድንበር አስከባሪ፤*

*ታሪክን ጠባቂ በሳል አገር መሪ፤*

*ቁም ነገር ከሥሩ ጥቂት ሳታስቀሪ፤*

*ሁሉንም ሸኝተሽ፤*

*ሁሉን አሰናብተሽ፤*

*እነማንን ወለድሽ ?!*

*እነማንን ተካሽ ?!*

*አገሬ ኢትዮጵያ እስቲ ልጠይቅሽ ?!*

*ለአገራቸውና ለወገናቸው ቁም ነገር ሠርተው ላለፉ ኢትዮጵያውያን በሙሉ መታሰቢያ ትሁንልኝ :: ታኅሳስ 24 2002 ዓ.ም. (January 2/ 2010)*

asradew@live.fr